# ጥምቀትና ከአምላክ ጋር ያለህ ዝምድና (ክፍል 1)

ይህ ትምህርት የተመሠረተው ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው? በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ 12 ላይ ሲሆን መጽሐፉ jw.org/am ላይም ይገኛል።

**ዓላማው፦ ምን ብለህ እንደምታምንና እንዲህ ያለ እምነት ልታዳብር የቻልክበትን ምክንያት ፈትሸህ ለማወቅ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምርና እምነትህን ለሌሎች ማስረዳት የምትችለው እንዴት እንደሆነ ለመመርመር።**



## ክርስቲያኖች መጠመቅ አለባቸው?

### 1 እምነትህን ፈትሽ

አንዳንድ ሰዎች አዎ የሚሉት ለምንድን ነው?

______________________________

______________________________

አንዳንድ ሰዎች አይ የሚሉት ለምንድን ነው?

______________________________

______________________________

አንተስ ምን ብለህ ታምናለህ?

______________________________

እንዲህ ብለህ እንድታምን ያደረገህ ምንድን ነው?

______________________________

______________________________



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 2 መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር መርምር

**ክርስቲያኖች ሙሉ በሙሉ ውኃ ውስጥ በመግባት መጠመቅ አለባቸው።**
(*የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት* የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 18 ከአንቀጽ 1-4 ተመልከት።)

### ማቴዎስ 28:19ን እና የሐዋርያት ሥራ 8:35, 36ን አንብብ።

የክርስቶስ ተከታዮች እንዲጠመቁ የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

### መዝሙር 40:7, 8 ን አንብብ።

ለመጠመቅ እያሰበ ያለ አንድ ሰው የአምላክን ፈቃድ ስለማድረግ ምን አመለካከት ሊኖረው ይገባል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________



**አንድ ጥበበኛ ሰው ቤቱን ከመገንባቱ በፊት ሥራው ምን እንደሚያካትት ለመገንዘብ እቅዱን ይመረምራል። በተመሳሳይም አንድ ጥበበኛ ሰው ከመጠመቁ በፊት አምላክ ምን እንደሚፈልግበት ለመረዳት የአምላክን ቃል ይመረምራል።— ሉቃስ 14:27-30**



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## ከመጠመቃችን በፊት ትክክለኛ እውቀት እና እምነት ሊኖረን ይገባል።

(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 18 ከአንቀጽ 5-7 ተመልከት።)

**ዕብራውያን 5:12 ን አንብብ።**

ከመጠመቅህ በፊት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል ማወቅ ይኖርብሃል?

**የሐዋርያት ሥራ 4:12ን፣ 2 ጢሞቴዎስ 3:16, 17ን እና ዕብራውያን 11:6ን አንብብ።**

ለጥምቀት ብቁ መሆን የምትችለው የትኞቹን ነገሮች አምነህ ከተቀበልክ ነው?

እውቀትህን ለማሳደግ እንዲሁም እምነትህን ለመገንባት ምን ነገሮችን ልታደርግ ትችላለህ? ምሳሌ ስጥ።



www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 3 እምነትህን ለሌሎች አስረዳ

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**ሕፃን ልጅ የሚጠመቀው አምላክ ከኃጢአቱ እንዲያነጻው ነው።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**በርካታ ሰዎች በዚህ ሐሳብ ይስማሙ ይሆናል። እኔ ግን ከዚህ የተለየ አመለካከት አለኝ፤ ምክንያቱም . . .**

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ እስከተቀበልከው ድረስ መጠመቅ ትችላለህ።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**እርግጥ በኢየሱስ ማመን አስፈላጊ ነው። ሆኖም መጠመቅን የመሰለ አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ ከዚያ ያለፈ ነገር እንደሚያስፈልግ ይሰማኛል። ምክንያቱም . . .**

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?


www.jw.org/am © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania